LAW Legal Action Worldwide

Debevoise & Plimpton

*Embargoed*

**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**የትግራይ ግጭት ሰለባዎች በጀርመን የመጀመርያው የወንጀል ክስ በከፍተኛ የኢትዮጵያ እና የኤርትራ መንግስታት እና ወታደራዊ ባለስልጣናት ላይ**

በርሊን፣ መጋቢት 11፣ 2017

በትግራይ ኢትዮጵያ ከተረሳው ግጭት የተረፉ 8 ሰዎች የቀድሞ የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኛ እና የቀድሞ ጊዜያዊ የመንግስት ባለስልጣን የሚገኙባቸው በ 12 የኢትዮጵያ እና የኤርትራ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እና የጦር መኮንኖች በግጭቱ ወቅት የጦር ወንጀል እና በሰው ልጆች ላይ ወንጀል ፈጽመዋል ሲሉ ለጀርመን ፌደራል አቃቤ ህግ ከባድ የወንጀል ክስ አቅርበዋል።

እነዚህ ተጎጂዎች ፣ ልክ እንደ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ፣ የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች እና ምስክሮች፣ የዘፈቀደ እስራት፣ ስቃይ እና ረሃብ ሰለባዎች ናቸው፣ እናም እስካሁን ድረስ ለደረሰባቸው ስቃይ ፍትህ ማግኘት ተነፍገዋል። ከተጠያቂነት ብቸኛ ተስፋቸው መካከል አንዱ የሆነው እነዚህ በሕይወት የተረፉት፣ አንዳንዶቹ በአሁኑ ጊዜ በጀርመን የሚኖሩ፣ የጀርመን ፌደራል አቃቤ ህግ በእነዚህ ወንጀሎች ላይ ምርመራ እንዲከፍት ጠይቀዋል።

እ.ኤ.አ. ከህዳር 2012 ጀምሮ በትግራይ ያለው ግጭት በግዳጅ ረሃብ፣ የሰብአዊ እርዳታ እገዳዎች፣ እልቂቶች፣ ጾታዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ ማሰቃየት እና የዘፈቀደ እስራትን ጨምሮ በጭካኔ በተፈጸሙ ክሶች ተለይቶ ይታወቃል። እነዚህ ጥሰቶች እና በደል በአብዛኛው በትግራይ ሰላማዊ ዜጎች ላይ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ ሃይሎች እንዲሁም በተባባሪ ሚሊሻ ቡድኖች የተፈፀሙ ቢሆንም በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉ ሌሎች አካላት እና የሌላ ብሄር ተወላጆች ሰላማዊ ዜጎችም ጭምር ናቸው። በሰፊው የተጠቀሰ አንድ ምንጭ በግጭቱን የሞት ቁጥር ከ 300,000 እስከ 800,000 ሰዎች መካከል አድርጎ አስቀምጧል።

ስምንቱ የትግራይ ተወላጆች ያቀረቡት አቤቱታ ለአንዳንዶቹ ግፍ ተጠያቂ ለማድረግ ሞክረዋል። ክሱ የተዘጋጀው በተወካዮቻቸው Legal Action Worldwide (LAW) እና ዶ/ር አና ኦህሚችን ሲሆን። በ eboise & LLP እና ከአውሮፓ የሕገ መንግስት እና የሰብአዊ መብቶች ማእከል (ECCHR) ድጋፍ ጋር በመሆን ለጀርመን ፌዴራል የህዝብ አቃቤ ህግ የተጠረጠሩትን ወንጀሎች ምርመራ እንዲከፍት ጠይቋል። በአለም አቀፍ የህግ ክለላ የዳኝነት ህጋዊ መርህ መሰረት መንግስታት በስር ባህሪው አስከፊ ወንጀሎች ምክንያት በውጭ ሀገር የሚፈጸሙ አለም አቀፍ ወንጀሎችን ክስ እንዲመሰርቱ ያስችላቸዋል።

የጀርመን ባለስልጣናት በሶሪያ፣ በጋምቢያ እና በኢራቅ የተፈፀሙ የጭካኔ ወንጀሎችን ለመክሰስ የአለምአቀፍ ሕግጋት ስልጣንን መርህ በተሳካ ሁኔታ ተጠቅመዋል። የትግራይ ተወላጅ ተጎጂዎች በአሁኑ ጊዜ የራሳቸውን ቀን በፍርድ ቤት እየጠየቁ ነው። ቅሬታው ወደ ምርመራው ከቀጠለ፣ እንዲህ ዓይነት ምርመራ ሲደረግ የመጀመሪያው ይሆናል።

**የLegal Action Worldwide ዋና ዳይሬክተር አንቶኒያ ሙልቬይ፣** *'በኢትዮጵያ በተከሰተው ግጭቶች ታይቶ በማይታወቅ የ ጭካኔ ደረጃ የታየበት ነበር። ሆኖም ከፍተኛ ግጭቶች ካበቁ ከሁለት ዓመታት በላይ ተጎጂዎች ተጠያቂ የሆኑትን ሰዎች ለማየት አልተቃረቡም። በተጎጂዎች ጥንካሬ እና ክትትል ዓለም እንዲሰማ እና እርምጃ እንዲወስድ ሲማጸኑ ዛሬ ፍትህን ለማስፈን በሚያደርጉት ጥረት ወሳኝ ቀን ነው።*

**የዴቤቮይስ እና ፕሊምፕተን LLP የአለም አቀፍ አለመግባባቶች አፈታት እና የህዝብ አለም አቀፍ ህግ ቡድኖች ተባባሪ ሊቀመንበር ካትሪን አሚርፋር** *"በትግራይ በተረሰ የጦርነት ሰለባዎች ወክለው ተጠያቂነትን ለመጠየቅ ከ LAW ጋር በድጋሚ አጋር መሆናችንን እናከብራለን። ኢትዮጵያ ወንጀለኞችን በአገር ውስጥ በህግ ተጠያቂ ለማድረግ ባለመቻሏ፣ የጀርመን ፌደራል አቃቤ ህግ ለእነዚህ አሰቃቂ ወንጀሎች ተጠያቂ የሆኑትን አጣርቶ ለፍርድ እንዲቀርብ ያቀረብነውን ጥሪ ተቀብሎ እንደሚያከብር ተስፋ እናደርጋለን።'*

**የኦህሚችን ኢንተርናሽናል መስራች ዶ/ር አና ኦህሚችን፣** *'በትግራይ የተፈፀመው ጥፋት መጠንና መጠን - ከ300,000 እስከ 800,000 ሞት! - አስደንጋጭ ነው። እነዚህ ወንጀሎች ተጣርተው ለህግ መቅረብ አለባቸው፤ ሌላው ቀርቶ አሁንም እየታዩ ያሉትን የአለም አቀፍ ህግ ጥሰቶችን ለማስቆም እና ሌሎች የአለም መሪዎችም ተመሳሳይ አሰቃቂ ወንጀሎችን እንዳይፈጽሙ ለመከላከል ነው። LAW ምስጋናይደረሰው እናግጭቱ እና በዙሪያው ያሉ ሁኔታዎች እንዲሁም አንዳንድ የተለዩ ጥፋቶች በትጋት ተመርምረው ለጀርመን ፌደራል የህዝብ አቃቤ ህግ ትኩረት አቅርበዋል ። የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ለዚህ ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ቅድሚያ እንደሚሰጥ እናምናለን።'*

**የዓለም አቀፍ ወንጀሎች እና ተጠያቂነት ፕሮግራም ECCHR ተባባሪ ዳይሬክተር አንድሪያስ ሹለር** *እንዳሉት "እንደሌሎች ግጭቶች ሁሉ ተጠቂዎች እና ምስክሮች በጀርመን ይኖራሉ። የጀርመን አቃብያነ ህጎች የምርመራ ማስረጃዎች በመያዝ ምርመራቸዎን ማከናወን እና ከሃገር ውጭ ለተፍፀሙ ወንጀሎችንም በአለም አቀፍ የ ወንጀል ምርመራ መርሕ ማጣራት ይኖርባቸዋል።'*

የጀርባ ማስታወሻዎች

**ይህ በLAW እና በባልደረባው ደብቮይስ እና ፕሊምፕተን LLP የትግራይ ተጎጂዎችን ወክለው ያቀረቡት ሁለተኛው አቤቱታ ሲሆን የመጀመሪያው ለአፍሪካ የሰብአዊ እና ህዝቦች መብት ኮሚሽን ከፓን አፍሪካ የህግ ባለሙያዎች ህብረት (PALU) ጋር በመተባበር የቀረበ ነው። የአፍሪካ ኮሚሽን ኮሙዩኒኬሽን በግጭቱ ወቅት በአፍሪካ የሰብአዊ እና ህዝቦች መብት ቻርተር የተጣለበትን ግዴታ ተጥሷል በሚል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ላይ ክስ ቀርቦ ነበር። እ.ኤ.አ ጥቅምት 2014 የአፍሪካ ኮሚሽን አስቸኳይ ጊዜያዊ እርምጃዎችን አውጥቷል፣ ኢትዮጵያ ማንኛውንም የህግ ጥሰት፣ የዘፈቀደ ግድያ እና ፆታዊ ጥቃትን እንድታቆም እና በትግራይ ሰብአዊ ተደራሽነት እንድታረጋግጥ አሳስቧል።**

**በጀርመን ያለው ክስ በ መስከረም 2016 ለፌደራል የህዝብ አቃቤ ህግ ፅህፈት ቤት ቀረበ እና በሌላ የማስረጃ መዝገብ [13 መጋቢት 2017] እየተጨመረ ነው። የጀርመን ፌዴራል አቃቤ ህግ ወደ እሱ የቀረቡ የወንጀሎች ክሶች ላይ መዋቅራዊ ምርመራን ለመክፈት፣ ወንጀለኞችን በተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ የወንጀል ምርመራ የማካሄድ ፣ የእስር ማዘዣ እንዲወጣ የመጠየቅ እና የወንጀል ክስ የመመስረት አቅም አለው።**

---

ለሚዲያ ቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች፣ እባክዎን groh@legalactionworldwide.org ያግኙን

LAW ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ የሰብአዊ መብት ጠበቆች እና የህግ ባለሙያዎች ደካማ እና ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚሰሩ ድርጅት ነው። በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅ እና በደቡብ እስያ የሰብአዊ መብት ረገጣ እና በደል ለደረሰባቸው ተጎጂዎች እና ማህበረሰቦች የህግ ድጋፍ ይሰጣል።

ዶ/ር አና ኦህሚችን፣ ሬክትሳንዋልቲን፣ በበርሊን የተመሰረተ የወንጀል ህግ ድርጅት ልዩ፣ ኢንተር አሊያ፣ በአለም አቀፍ የወንጀል ህግ፣ በሰብአዊ መብቶች እና በወንጀል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ትብብር ኦህሚችን ኢንተርናሽናል መስራች ናቸው።

ዴቤቮይስ እና ፕሊምፕተን LLP  ዋና መሥሪያ ቤቱን በኒውዮርክ ያደረገ ዓለም አቀፍ የሕግ ድርጅት ሲሆን ሰፊ የሕዝብ ዓለም አቀፍ ሕግ አሠራር ያለው፣ በክልላዊ እና ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች እና ፍርድ ቤቶች ፊት ፓርቲዎችን መወከልን ጨምሮ ይቀርባል። ዴቤቮይስ በእነዚህ ሂደቶች ለ LAW ድጋፍ ሰጪ አማካሪ ነው።

ECCHR በበርሊን ላይ የተመሰረተ ነጻ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ የህግ እና ትምህርታዊ ድርጅት በአለም አቀፍ ደረጃ የሲቪል እና የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የሚሰራ ድርጅት ነው።  በ1999 በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጠበቆች የተቋቋመው በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እንዲሁም በሌሎች የሰብአዊ መብቶች መግለጫዎችና ብሄራዊ ህገ-መንግስቶች የተረጋገጡ መብቶችን በህጋዊ መንገድ ለመጠበቅ እና ለማስከበር ነው።